# የቀበሮ ባሕታዊ በበጎች መካከል ይሰግዳል

ባለፈው ሰሞን ዋሽንግተን ዲሲ ላይ በተደረገው የእግር ኳስ ጨዋታ ዝግጅት የፖለቲካ ድርጅቶችም በየበኩላቸው ስብሰባ ጠርተው ደጋፊዎቻቸውን አነጋግረዋል:: የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ሁሉ በሚፈልገው የትግል መስመር ለመሳተፍ የሚያስችለውን መንገድ ለማየት እድል ሰጥቶታል::

ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲና የሕግ የበላይነት ይሰፍን ዘንድ ወያኔን የሚቃወሙ ሃይሎች የሚያደርጉትን ጥረት በአንክሮ ተከታትያለሁ። አስመሳዮችን፣ አንጋሾችንና የፖለቲካ ደላላዎችን ታዝቤያለሁ። በተቃዋሚነት ስም ለትግሉ ትልቅ መሰናክል የደነቀሩ ቡድኖች አይናቸውን በጨው ታጥበው ድጋፉችሁን ለግሱን ሲሉ ተመልክቻለሁ።

"አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ" ፓርቲን ለማስተዋወቅ ከኢትዮጵያ መጥተው ስብሰባ የጠሩትን ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምን በቅጡ ታዝቤአቸዋለሁ። አናሳ የነበረውና ራሱን ባግባቡ ሳያደራጅ ከተደራጁና ካድራጁ ፓርቲዎች ጋር የተቀላቀለውን የቀስተ ደመናን ፓርቲ ከዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ጋር ከመሩ በኋላ ሁለቱ በነበራቸው ሽኩቻ ሲነታረኩ ከርመዋል። የዶክተሩ ብርሃኑን የሾኬ ጠለፋ ሊቋቋሙ ባለመቻላቸው ራሳቸው እንደገለጹት የስንብት ደብዳቤ ጽፈው ነበር።

ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም ከሚያስተምሩበት ከሙያቸው ውጭ ባላቸው የፖለቲካ አመለካከታቸውና አካሄዳቸው ብዙ ኢትዮጵያውያን አያምኗቸውም:: አስመሳይነት፣ አድርባይነት እና ግራ የሚያጋባ አቋም ሲያስተጋቡ ስለታዩ በእርሳቸው ላይ እምነት የላቸውም:: ገና በአጼ ኃይለሥላሴ ሥርዓት መውደቅ ጀምሮ በደርግ ጊዜ ከበረከት ሀብተሥላሴ ጋር የመርማሪ ኮሚሽን አባል ሆነው ለ 60ዎቹ ሰዎች መገደል መሳሪያው በእጃችሁ ምን ትጠብቃላችሁ እያሉ ደርግን በመገፋፋትና አሳልፎ በመስጠት ተጠያቂ ናቸው:: ነገሩ ተሸፋፍኖ ቀረና:: የደርግ አገዛዝ ሊወድቅ ሲቃረብ ደግሞ ከወያኔዎች ጋር በመሆን ወያኔዎች ሲገቡ ይደገፉ እንደነበር አይዘነጋም:: በወያኔም የዘረኝነትና የአምባገነን አገዛዝ ውስጥ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ነኝ ከማለት እና የሚሞተውን፣ የቆሰለውንና የታሰረውን ከመመዝገብ በቀር ያደረጉት ይህ ነው የሚባል ተቃውሞ ሲያሳዩ በጭራሽ አልታዩም:: ለኢትዮጵያም ይሄን ሰሩ ሊባል የሚችል ነገር አንዳችም አልፈየዱም:: ያው በዘወትር ንግግራቸው ሁለት ትርጉም ያለው ወይም ለአድማጭ ግራ የሚያጋባ አባባልና አነጋገር መወርወራቸው የተለመደ ባህርያቸው ነው::

ፕሮፌሰር መሥፍን ከጥቂት ዓመታት በፊት አገር ቤት እያሉ የወያኔ ህዝብ ደህንነት ኃላፊ የነበረውና መለስ ዜናዊ ያስገደለውን ክንፈ ገብረመድኅን ጓደኛቸው እንደነበረ እየደጋገሙ ሲነግሩን ነበር ጓደኛቸውን ታዲያ ምነው አገር አታጥፉ ሕዝብ አትከፋፍሉ አትግደሉ ብለው አልነገሩት ?

የኢሰመጉ መሪ በነበሩበት ወቅት ወያኔ አፍኖ ይሙቱ ይኑሩ ሳይታወቅ ጠፍተው የቀሩትን የኢሕአፓ አባላት አንድም ቀን በሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቱ የጠፉ ወይም የተገደሉ በሚለው ላይ ሳያስመዘግቡና የወያኔ ወንጀል ተሸፋፍኖ እንዲቀር ያደረጉት ሚና የሚዘነጋም አይደለ፤

ዛሬ ደግሞ ወያኔ ጠላታችን አይደለም እያሉ በአሜሪካ እየተዘዋወሩ መስበካቸው ምን ማለት ነው? ታዲያ ጠ ላታችን ማነው? አገር የገነጣጠለው፣ ወደብ አልባ ያደረገን፣ ዘረኝነትን የሚያራምድ፣ የኢትዮጵያን ተቋሞች ያፈራረሰ፣ ምርጫ ያጭበረበረ፣ ብዙ ንጹሐን ዜጎችን የገደለ ያስገደለ፤ አገሪቱን ለረሃብና ለበሽታ ያጋለጠ፣ የሕዝብ ሀብት የአገር ሀብት የዘረፈና ያዘረፈ ጠላት ካልተባለ ማን ሊባል ነው?

ፕሮፌሰር መሥፍን እኛ ያለወያኔ ወያኔም ያለ እኛ መኖር አይችልም እያሉ የሚሰብኩ የ80 ዓመት አዛውንት ከመጃጀት ነው ወይስ ለቀረችው ጥቂት ዓመታት ለመኖር ሲሉ የወያኔን እድሜ ለማራዘም? በውጭ ኃይል በኩል የተሰጣቸውን ሚሽን ለመጨረስ ነው? ፍርሃትን አድርባይነትን ተገዥነትን አውርሰው ለመሞት ከፈለጉ የሚቀበላቸው የለም በእድሜያቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ አሳዝነውና ከድሮው ጀምሮ ላደረጉት ድርጊት ይቅርታ ሳይጠይቁ ዛሬ በሕዝብ መሀል ተገኝተው ብርቱካን ትምራችሁ ይሉናል:: አሳዛኝና አሳፋሪ ነገር ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመራውን ይመርጣል ወይም ምራኝ ይላል የፈለገውምን እንጂ እንጂ ፕሮፌሰር መሥፍን አይመርጡለትም:: የወያኔን እድሜ በተቃዋሚ ስም ሆነው ለመቀጠል መሞከራቸው ነው:: ወያኔ እንደሆነ ተለማመጡት ለመኑት አለመኑት አገር ማጥፋቱን አይተውም:: በነገራችን ላይ የቅንጅት መሪዎች ከቃሊቲ ከመውጣታቸው በፊት የዶክተር ብርሃኑ ባለቤትና የፕሮፌሰር መሥፍን ልጅ ከአሜሪካ ከቦስተን የሄደችው በየጊዜው ወያኔ ቤተመንግሥት ይመላለሱ እንደነበር ያደባባይ

ምስጢር ነበር። ወያኔ ቤተመንግሥት ሲያስኬዳቸው የነበረው ጉዳይ፡ አሁን ግልጽ እየሆነልን መጣ። ከኢትዮጵያ ሕዝብ መቼም ተደብቆ የሚቀር ነገር የለም።

የአመራሩ አባላት ከእስራት ከተፈቱ በኋላ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የፈጠረውን ትርምስ በሚመለከት የቅንጅት ደጋፊዎችና የኢትዮጵያ ህዝብ የፕሮፈሰሩን አዛውንታዊ አስtያየት ይጠብቅ ነበር። "ብርቱካንን ተከተሏት" የሚል መመርያ ሰጡን። ወ/ሮ ብርቱካን የህዝብ ተመራጭ አለመሆኗንና ወደ ቅንጅት አምሻሽታ የመጣች የዶ/ር ብርሃኑን የቤት ስራ ለማከናወን መሆኑን እንተወውና ህዝብና የቅንጅት ፓርቲ አመራር የመረጣቸው ፕረዚዴንቱን ትተው ምክትሏን እንድንከተል "መመሪያ" የሚሰጡን ለምን ይሆን? በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠ ታማኝ መሪ እያለ እርሳቸው የመረጡልንን ኋመሪቃ እንድንከተል ሲነግሩን የዴሞክራሲን መሰረታዊ መርህ መቃረን አይሆንባቸውምንሕ ይባስ ብለው ወሐሮ ብርቱካንና ከቅንጅት የከዱ ግብረ አበሮቿ ያቋቋሙትን አንጃ ሲያተናክሩ የአንጃው ፕሬዚዴንት ኢንጂነር ሃይሉ ናቸው አሉን። አፈንጋጮች ላቋቋሙት አንጃ ፓርቲ ኢንጂነር ሃይሉ እንዴት ፕረዚዴንት ሊሆኑ እንድሚችሉ መገምት አስቸግረን። ፕሮፈሰሩ የሚያሾፉም መሰለን። አንጃው ለወያኔ መሳሪያ በመሆን የህዝብን የነጻነት ትግል ማዳከሚያ አልሆነም ወይ? የሚል ምስረታዊ ጥያቄ ተደጋግሞ ተጠይቋል።

የመጡበትን የአንጋሽነት (king maker) ሚናቸው ላይ በማተኮር ወ/ሮ ብርቱካን ሎጋ ለግላጋ ወጣት መሆኗን አውስተው ከሴናተር ኦባማ ጋር ሊያወዳድሯት ቃጣቸው። አንድ ታዛቢ ኦባማ የ47 አመት ሰው መሆኑንና ወ/ሮ ብርቱካን ግን 34 አመት እንደሆነች ሲጠቅስላቸው ላለመረታት ብለው ሁለቱም ህግ አጥንተዋል ብለዋል። ወ/ሮ ብርቱካን ለወያኔ ፍ/ቤት ዳኝነት ለመሾም የወያኔ ግፈኛ ስርአት የሚፈልገውን መስፈርት አሳምራ ያሟላች መኖሯን እንተወውና ሰሜን አመሪካ መጥታ የነበረ ጊዜ በየቦታው ከሰጠችው ዲስኩር እንደተረዳነው እንኳን የህግ ምሩቅ በህግ ትሐቤት በራፍ አጠገብ ያለፈችም አትመስል።

ፕሮፌሰሩ ወያኔዎች ላደረሱት ጥፋት ይቅርታ እናድርግላቸው፣ የዘረፉትንም ሀብትና ንብረት እንተውላቸው አንዴ ሆኗል ይሉናል። እረ በህግ አምላክ ፕሮፌሰር መሥፍን ወያኔ ትላንት ለገደላቸው ሰዎች ይቅርታ ሊጠይቅ ቀርቶ እናንተን አይደለም እንዴ ይቅርታ ያስጠየቀው፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ አይደለም እንዴ ለምን በምርጫ ጣላችሁኝ ብሎ አሳር ስቃዩን የሚያሳየው በረሃብና በችግር የሚቆላው፡ እርስዎ የምን ቤት ነዎት ለወያኔ ይቅርታ ጠያቂ የሆኑት በዚህ ዓይነት ብርቱካንንም የትግራይን ሕዝብ ይቅርታ ጠይቂ ብለው የመከሯት እርስዎ ሳይሆኑ እንዳልቀረ ያስጠረጥራል።

ተፋፍሞ የተቀጣጠለው የህዝብ የነጻነት ትግል ተጠናክሮ እንዲቀጥል በማድረግ ፈንታ እንዲከፋፈልና እንዲዳከም ሲጥሩ ነው እስከዛሬ የተመለከትነው።

እርሳቸውና በዋሽንግተን አካባቢ የሚኖሩ የአንጃው ደጋፊዎች የጠሩት ስብሰባ የተጀመረው በጸሎት ነበር። በመካከላችሁ ልጸልይ ብለው በጠየቁት ያልተለመደ ጥያቄ መሰረት ተሰብሳቢውን አንገቱን አስደፍተው ፕሮፈሰሩ እንደ ካህን ሆነው ጨክ ብለው ጸለዩ። መጸለያቸው ባልከፋ። ከልባቸው ጸልየው ይሆን ወይስ የታዳሚውን አንጀት ለመብላት ያዘጋጁትን ይሆን ያወረዱልን? ለብዙዎቻችን ቅንነት የተመላበት ጸሎት አልነበረም። የሚፈጽሙት የመሰሪነት ተግባርና በጸሎት ያስሙን አይጣጣምም። ተሰብሳቢውን ተላላና በግ አድርገውታል። "የቀበሮ ባሕታዊ ከበጎች መካከል ይሰግዳል" ይሏል ይህ ነው።

ተላላዎች ሁል ጊዜም የመሰሪዎች መጫወቻዎች ናቸው። አንድነታችን እየተናደ ያለው ተወናባጅ በመሆናችን ነው። ፕሮፈሰሩ -በቅጽል ስማቸው ("ፕሮፈሰር ተንኮሉ") የተሰብሳቢውን የማሰብ ችሎታ ንቀውታል። በዚህ እድሚያቸው ያወናብዳሉ። እኛ ደግሞ መወናበድ የለብንም። ከሀቀኛ ተቃዋሚዎች ጎን በመቆም እነዚህ የወያኔን እድሜ የሚያራዝሙትን መቃወም አለብን።

የወያኔን እድሜ የሚያራዝሙ ታማኝ ተቃዋሚዎችን እንቃወማቸው!
ኢትዮጵያ በቆራጥና በሀቀኛ ልጆቿ ትግል ነጻ ትወጣለች!

ሰለሞን አሰፋ
ከዋሽንግተን ዲሲ